
الامهرية
አማርኛ

# 2 የውድዕ አደራረግ የተይሙምና የገላ አስተጣጠብ ሁኔታ

## የውድዕ አደራረግ


1
በልቡ ውዱዕ ለማድረግ ይነይታል ከዚያም እንዲህ ይላል : ቢስሚላህ በመቀጠል መዳፎችን ያጥባል




2
በቀኝ መዳፍ እጁ ውሃን በማድረግ (አፉን ይጉመጠመጣል ያመላልሠዋል);ከዚያም ይተፈዋል *ውሃ ይዞ ኢስቲንሻቅ ያደርጋል በአፋንጫው ይስበዋል*ከዚያም * በግራ እጁ አውራ ጣቱንና አመልካች ጣቱን አፋንጨውን በመያዝ የገባውን ውሃ ያስወጣዋል.



3
ከዚያም ፊቱን *በተለምዶ ከጭንቅላቱ የፀጉር ማብቀያ አንስቶ እስከ የፂም ማብቀያ መጨረሻ ድረስ አገጩን ጨምሮ ወደ ታች; ወደ ጉን ደግሞ ከጆሮ ጥግ እስከ ሌላኛው የጆሮ ጥግ ያጥበዋል*



4
ከዚያም እጆቹን ከጫፉ ጣቶቹ አንስቶ እስከ ክርኖቹ ቀኙን ቀጥሎ ግራውን ያጥባል.




5
ከዚያም ሙሉ በሙሉ የራሡን ፀጉር ያብሣል እጁን ከፊትለፊት ፀጉር አንስቶ ወደ ማጅራቱ ወስዶ ይመልስዋል.



6
አመልካች ጣቶቹን በጆሮ ውስጥ በማስገባት ያሻቸዋል በአውራ ጣቱም የላይኛውን የጆሮ ክፍል ያብሳል.



7
ከዚያም ቀኙን በማስቀደም ሁለት እግሮቹን እስከ ቁርጭምጭሚቱ ያጥባል.



8
-*ከተወሰነው የአስተጣጠበብ መጠነን መጨመር እንዴት ይታያል* በውድዕ ላይ ከተደነገገው ትጥበት መጨመር አይቻልም' ከሥስት በላይና ከእጆቹ ጡንቻዎች ከፍ አድርጉ ማጠብ መጨመርና የእግሩን ባት ከቁርጭሚት ከፍ አድርጉ ማጠብ አልያም ማጅራቱን ማበስ አይፈቀድም.



9
-ውድዑን ከጨረስ ቡሃላ የሚለው ድዓ:"አሽሃድአላኢላሀ ኢለላሀ ዋሀደሁ ላሸሪከለሁ ; ወአሽሃድ አነ ሙሐመደን አብድሁ ወረሱሉሁ ".
በቲርሚዚ ዘገባ -" አላሁመ ኢጀአልኒ ሚነ ተዋቢን ወጅአልኒ ሚነ ሙተጣሂሪን ".

10
-ውድዕን የሚያጠፋ
1-ከሁለት ቀዳዳዎች የሚወጣው ሽንት አይነ ምድርና ፈስ.
2-ተይሙም ማለት : የውድዕ ምትክ ሲሆን ውሃን በስውነታችን ለመጠቀም ካልተቻለ ውሃን ባለማግኘት ወይም አደጋ ይደርስብኛል ብሎ ከስጋና ከፈራ ' ያን ጊዜ አፈርን እንደ ውሃ መጠቀም ይችላል
3-የግመል ሥጋ መብላት


## የተይሙም አደራረግ

1
ተየሙምን በቀልቡ ይነያና ከዚያም "ቢስሚላህ"ይበል ቀጥሎም መሬቱን ( አፈሩን ) በእጆቹ አንዴ መታ በማድረግ ፊቱን እና የእጆቹን መዳፎች የውጨኛ ክፍል ይበስ

2
ተየሙምን በቀልቡ ይነያና ከዚያም "ቢስሚላህ"ይበል ቀጥሎም መሬቱን ( አፈሩን ) በእጆቹ አንዴ መታ በማድረግ ፊቱን እና የእጆቹን መዳፎች የውጨኛ ክፍል ይበስ




3
-አፈሩን በምንመታበት ጊዜ- ጣቶችን መዘረጋትና በመሃከላቸው አፈሩን ማዳረስ ግድ አይሆንም.



## ግዴታዊ የገላ ትጥበት ሁኔታ

1
በልቡ መታጠብን ይነይታል በድብቅም (በዝቅተኛ ድምፅ) ቢስሚላህ ይላል ከዚያም ጠቅላላ ስውነቱን ውሃ ያዳርሣል ቀላልና ብዙ ፀጉር ያለበትን ክፍሎች በደንብ በውሃ ያስራጫል በሙጉመጥመጥና በአፍንጫ ውሃን በመሣብ አዳርሶ ያጥባል.

2
መታጠብን ግዴታ የሚያደርጉ።
1. ጀናባ : ሚስትን መገናኘት የዘር ፈሣሽን ማፍስስ ይኖርበታል ወይም ብልትና ብልት መነካካት2-የወር አበባና የወሊድ ደም መፈስስ.
3-መስወዓት (ሸሒድ) ያልሆነ ሟች 4- ካፌር እስልምናን ሲቀበል ።

-አዘጋጅ :ዶ/ሐይስም ስርሐን ' በመስጂደ አነበዊ አስተማሪና "በሡና መአሃድ ሃላፊ:" http://mahadsunnah.com

ፓንፐሌቶችን ለመቶርገም sarhaan.com